ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ
አውቃፍ ሚኒስትር

ጁማዳል አኺራህ 6/1441 ሂ.
ጃንዮሪ 31/2020 ግ.

# የቁርጠኝነት ጥንካሬ የሰለጠኑ ህዝቦች የእድገት መሰረት ነው

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ

**سَابِقُوا إِلَى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا كَعَرْض السَّمَاءِ وَالْأَرْض أُعِدَّتْ لِلَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرُسُلِهِ ذَلِكَ فَضْلُ اللَّهِ يُؤْتِيهِ مَنْ يَشَاءُ وَاللَّهُ ذُو الْفَضْلِ الْعَظِيمِ}**

ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነችም ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡ ለእነዚያ በአላህና በመልክተኞቹ ላመኑት ተዘጋጅታለች፡፡ ይህ የአላህ ችሮታ ነው፡፡ ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል፡፡ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው፡፡) ማለት ነው፡፡
ብቸኛ ከሆነው ለሱም አጋሪ ከለለው አላህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ፡፡ እንዲሁም ሰይዲና ሙሐመድም የሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካም ምግባር በተከተሏቸው ምእምናን እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን አውርድ፡፡

**ከዚህም በመቀጠል፡**

የእስልምና ሃይማኖት የላቁ በሆኑት አስተምህሮዎቹ የሰው ልጅ ቁርጠኛ፣ ታታሪና ለልማት የሚጣጣር እንዲሆን ይገፋፋል፡፡ በአንፃሩም ስንፍናን፣ ዝለትንና ማበላሸትን እንዲርቅ ያስገነዝባል፡፡ ይህም ተግባር የቀደምት መልክተኞች መልእክት እንደነበረ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ሲል አመልክቷል፡፡

**أَمْ لَمْ يُنَبَّأْ بِمَا فِي صُحُفِ مُوسَى * وَإِبْرَاهِيمَ الَّذِي وَفَّى * أَلَّا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَى *وَأَنْ لَيْسَ لِلْإِنْسَان إِلَّا مَا سَعَى *وَأَنَّ سَعْيَهُ سَوْفَ يُرَى *ثُمَّ يُجْزَاهُ الْجَزَاءَ الْأَوْفَى}**

ትርጉሙም (ይልቁንም በዚያ በሙሳ ጽሑፎች ውስጥ ባለው ነገር አልተነገረምን? በዚያም (የታዘዘውን) በፈጸመው በኢብራሂም (ጽሑፎች ውስጥ ባለው አልተነገረምን?) (እርሱም ኃጢያት) ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ነፍስ ኃጢአት

አትሸከምም፡፡ ለሰውም ሁሉ የሠራው እንጅ ሌላ የለውም፡፡ ሥራውም ሁሉ ወደ ፊት ይታያል፡፡ ከዚያም ሙሉውን ምንዳ ይመነዳዋል፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የቁርጠኝነት ጥንካሬን ከፍተኛ ደረጃ እንዲህ በማት ገልጸውታል፡ (አላህ ቸር ነው፡፡ ቸርነትንም ይወዳል፡፡ የላቁ ስነ ምግባሮችንም ይወዳል፡፡ እርኩስ ምግባሮችን ደግሞ ይጠላል፡፡) (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) ዑመር ኢብን አልኸጣብ እንድህ ይላሉ፡ ‹ቁርጠኝነታችሁን (ወኒያችሁን) ዝቅ አታድርጉ፡፡ እኔ ከቁርጠኝነት ማነስ የበለጠ ክብርን ዝቅ የሚያደርግ ነገር አላየሁም፡፡› የጥንት አበውም ‹የቁርጠኝነት ጥንካሬ የአንድ ሰው አእምሮ ምሉእነት ምልክት ነው፡፡› ይሉ ነበር፡፡ አቡ አጠይብ እልሙተነቢ የተሰኘው የግጥም ደራሲ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡፡

ለሙሉነት ችሎታ እያላቸው ከሚያጎድሉ የከፋ ለሰዎች ነውር ምክኒት የሚሆን ነገር አይቸ አላውቅም፡፡

የቁርጠኝነት ጥንካሬ በተለየ መስክ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን አንድ ሰው በህይወቱ በሚያደርጋቸው ሁሉም ተግባራት እውን ሊሆን የሚገባ ተግባር ነው፡፡ የአስልምና መመሪያዎች የሰው ልጆች ወደበዒባዳ በፍጥነት እንዲያመሩና በዚህም መስክ እንዲሽቀዳደሙ ይገፋፋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَسارِعُوا إِلى مَغْفِرَةٍ مِنْ رَبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا السَّماواتُ وَالْأَرْضُ أُعِدَّتْ لِلْمُتَّقِينَ}

ትርጉሙም (ከጌታችሁ ወደ ኾነችም ምሕረትና ስፋትዋ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ኾነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትኾን ተቻኮሉ፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) በዒባዳ መስክ ለሚጣጣር ሰው መንዳውን የሚያበዛለት መሆኑን እንድህ በማለት ገልጹአል፡

{وَمَنْ أَرَادَ الْآخِرَةَ وَسَعَى لَهَا سَعْيَهَا وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَأُولَئِكَ كَانَ سَعْيُهُمْ مَشْكُورًا}

ትርጉሙም (መጨረሻይቱንም ዓለም የፈለገ ሰው እርሱ አማኝ ኾኖ ለርሷ (ተገቢ) ሥራዋን የሠራም ሰው እነዚህ ሥራቸው የተመሰገነ ይኾናል፡፡) ማለት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) በሕይወታቸው ሁሉ ጠንካራ ቁርጠኝነት ነበራቸው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ሲል አዟቸዋል፡

{يَا أَيُّهَا الْمُزَّمِّلُ قُمِ اللَّيْلَ إِلَّا قَلِيلًا نِصْفَهُ أَوِ انْقُصْ مِنْهُ قَلِيلًا *أَوْ زِدْ عَلَيْهِ وَرَتِّلِ الْقُرْآنَ تَرْتِيلًا إِنَّا سَنُلْقِي عَلَيْكَ قَوْلًا ثَقِيلًا}

ትርጉሙም (አንተ ተከናናቢው ሆይ፡፡ ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም፤ (ስገድ)፡፡ ግማሹን (ቁም)፤ ወይም ከርሱ ጥቂትን ቀንስ፡፡ ወይም በእርሱ ላይ ጨምር፡፡

ቁርአንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ፡፡ እኛ ባንተ ላይ ከባድ ቃልን እንጥላለንና፡፡) ማት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እግራቸው እስከሚሰነጠቅ ሌሊት ይሰግዱ ነበር፡፡ ለምን እንደዚህ ይሆናሉ ያለፈውንም የሚመጣውንም ወንጀለዎትን አላህ መህረት አድርጎለዎት እያለ ተብለው በተጠየቁ ጊዜም የሰጡት መልስ፡ (እጅጉን አመስጋኝ ባሪያ ልሆን አይገባኝምን? ) የሚል ነበር፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ባልደረቦቻቸውና መላ ህዝቦቻቸውም የተለየ የቁርጠኝነት ጥንካሬ እንድኖራቸው በተለያየ መልኩ ይገፋፉ ነበር፡፡ እንድህም ብለዋል፡ (አላህን በምትለምኑ ጊዜ ፊርደውስን ለምኑት፡፡ እሱ ከበላያ የአላህ ዐርሽ ያለና የጀነት ወንዞች የሚመነጩበት የጀነት ማእከላዊ ወይም የላይኛው ክፍል ነው፡፡) (ክርሳቸው አላህ ይውደድና) ረቢዓ አብን ካዕብ የተባሉት የነብያችን ባልደረባ እንድህ ይላሉ፡ ‹ብዙውን ጊዜ ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ጋር አድር ነበር አንድ ወቅት የውዱ ውሃና የሚያስፈልጉ ነገሮችን አቀረብኩላቸው፡፡ ያን ጊዜ (የምትፈልገውን ነገር ጠይቅኝ) አሉኝ፡፡ እኔም በጀነት ከርሰዎ ጋር መሆንን እፈልጋለሁ አልኩኝ፡፡ እሳቸውም (ከሱ ሌላ ነገር በጠየቅህኝ) አሉኝ፡፡ እኔም እሱን ብቻ ነው የምፈልገው አልኩኝ፡፡ ያን ጊዜ (እንግዳውስ ስግደት በማብዛት እገዘኝ) አሉኝ፡፡

በዒባዳ የቁርጠኝነት ጥንካሬ ስንል አሳምሮ ማከናውን ማለታችን ሲሆን ይህ ተግባር በአንድ ሰው የማይዋሽ፣ የማይክድ፣ የማያታልልና በከንቱ የሰዎችን ገንዘብ የማይበላ በመሆን በስነ ምግባሩና በአጠቃላይ ጸባዩ ጎልቶ ይታያል፡፡ በዚህም የዒባዳው ተግባር ከአላማው ጋር የተጣጣመ ይሆንና የእምነቱዋና አላማ የሆነው ቅንነት በሰውዬው ላይ እውን ይሆናል፡፡

የቁርጠኝነት ጥንካሬ የሚያስፈልገው ሌላው መስክ ደግሞ ትምህርት ነው፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) ፋይዳው የሰው ልጆችን የሚሸፍን የሆነን እውቅት ይሰጠን ዘንድ አላህን እንድንለምን እንድህ በማለት መክረውናል፡ (ጠቃሚ እውቀትን እንድሰጣችሁ አላህን ለምኑት፡፡ ከማይጠቅም እውቀት እንዲሰውራችሁ በአላህ ተጠበቁ፡፡)

ጠቃሚ የሆነ እውቀት ሀገራት ኃይል የሚያገኙበትና ህዝቦች የሚበለጽጉበት እውነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ያአደጉ አገሮች የእድገታቸው መሰረት አውቀት ሲሆን ወደኋላ የቀሩም ሀገራት የኋላ ቀርነታቸው ምክኒያት በእወቀት ዘርፍ ጠንካራ ጥረት ባለማድረጋቸው ነው፡፡

ባልደረቦችና ተከታዮቻቸውም እውቀትን በማካበት ጠንካራ ቁርጠኝነት ነበራቸው፡ ፡ እነሆ አቡ ሁረይራ የተባሉት ባልደረባ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹ከነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እውቀትን ከማግኘት በወንዝ አትክልትን መትከልም ሆነ በገበያ የመሸጥ መለወጥ ውል አያግደኝም ነበር፡፡ የአላህ መልክተኛ ቃላትን እንዲያስተምሩኝ እከታተል ነበር...› አብደላህ ኢብን ዓባስ የተባሉት ባልደረባ ደግሞ እንድህ ይሉ ነበር፡ ‹ከአንድ ሰው ዘንድ የነብያችን ሃዲስ መኖሩን በሰማሁ ጊዜ ቀን ላይ አረፍ ባለበት ወቅት ሄድኩ፡፡ እበሩም መጎናጸፊያን ተንተርሸ ጋደም አልኩኝ፡፡ ንፋስም አቧራን በፊቴ ላይ ነሰነሰብኝ፡፡ እሱም ተንስቶ ሲወጣ ባየኝ ጊዜ የአላህ መልክተኛ ሆይ! ምን አመጣህ?

ብትልክብኝ እኔ አለህበት እመጣ አልነበረም ወይ? አለኝ፡፡ እኔም አይደለም እኔ ነኝ ወዳለህበት መጥቼ ስለሐዲሱ መጠየቅ ያለብኝ አልኩት፡፡›

የቀደምት ዑለሞች በተለያዩ ዘርፎች እውቀትን በማከማቸትና መልእክቱንም ለቀጣዩ ትውልድ በማስተላለፍ የነበራቸው ታታሪነት ይህ ነው አይባልም ነበር፡፡ በዚህም ስማቸውን በታሪክ ማህደር በብርሃናዊ ፊደሎች አስመዝግበው አልፈዋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

فَأَمَّا الزَّبَدُ فَيَذْهَبُ جُفَاءً وَأَمَّا مَا يَنفَعُ النَّاسَ فَيَمْكُثُ فِي الْأَرْضِ}

ትርጉሙም (ኮረፋቱማ ግብስብስ ኾኖ ይጠፋል፡፡ ለሰዎች የሚጠቅመውማ በምድር ላይ ይቆያል፡፡ እንደዚሁ አላህ ምሳሌዎችን ይገልፃል፡፡) ማለት ነው፡፡

*ሥራን* በሚገባ ማከናውን የቁርጠኝነት ጥንካሬን የሚጠይቅ ሌላው መስከ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) *ሥራ* ከዒባዳ ጋር የተሳሰረ ተግባር መሆኑን እንድህ በማለት አመልክቷል፡

فَإِذَا قُضِيَتِ الصَّلَاةُ فَانتَشِرُوا فِي الْأَرْضِ وَابْتَغُوا مِن فَضْلِ اللَّهِ وَاذْكُرُوا اللَّهَ كَثِيراً لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ}

ትርጉሙም (ሶላቲቱም በተፈጸመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑ፡፡ ከአላህም ችሮታ ፈልጉ፡፡ አላህንም በብዙ አውሱ፡፡ ልትድኑ ይከጀላልና፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ሱ.ወ.) *ሥራውን* ለአሳመረ ሰው በዚህች ዓለም መልካም ሕይወት እንድሁም በመጭው ዓለም ዘላቂ ተድላ የሚሰጠው መሆኑንእንድህ በማለት ገልጹአል፡

{مَنْ عَمِلَ صَالِحاً مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَى وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُ حَيَاةً طَيِّبَةً وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ}

ትርጉሙም (ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፡፡ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን፡፡) ማለት ነው፡፡

إِنَّ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ كَانَتْ لَهُمْ جَنَّاتُ الْفِرْدَوْسِ نُزُلاً}

ትርጉሙም (እነዚያ ያመኑና መልካም *ሥራዎችን* የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው፡፡) ማለት ነው፡፡

ለ*ሥራ* ክብርነት ከጥንት ጀምሮ ነብያት በሙሉ ሰርተው ይበሉ የነበረ ከመሆኑ የበለጠ ማስረጃ አያስፈልገውም፡፡ አባታችን አደም፣ ኢብራሂምና ሉጥ አርሶ አደሮች

ነበሩ፡፡ ነብዩ ኑሕ አናጢ፣ ነብዩ ኢድሪስ ልብስ ሰፊ፣ ነብዩ ሷሊሕ ነጋዴ እንድሁም ነብዩ ዳዉድ ብረት ቀጥቃጭ ነበሩ፡፡ አላህ (ዐ.ወ.) እንድህ ይላል፡

**{وَلَقَدْ آتَيْنَا دَاوُودَ مِنَّا فَضْلًا يَا جِبَالُ أَوِّبِي مَعَهُ وَالطَّيْرَ وَأَلَنَّا لَهُ الْحَدِيدَ * أَنِ اعْمَلْ سَابِغَاتٍ وَقَدِّرْ فِي السَّرْدِ وَاعْمَلُوا صَالِحًا إِنِّي بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ}**

ትርጉሙም (ለዳውድም ከእኛ የኾነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፡፡ (አልንም)፡- «ተራራዎች ሆይ! ከእርሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ፡፡ በራሪዎችንም (ገራንለት)፡፡ ብረትንም ለእርሱ አለዘብንለት፡፡» ሰፋፊዎችን ጥሩሮች ሥራ፡፡ በአሠራርዋም መጥን፡፡ መልካምንም ሥራ ሥሩ፡፡ እኔ የምትሠሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና (አልነው)፡፡) ማለት ነው፡፡

ሥራ ክብር የሚኖረው ብጥራት ሲከናወን ብቻ መሆኑን ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እንድህ በማለት አብራርተዋል፡ (አንዳችሁ ሰጠውም ከለከለውም አንድን ሰው ከሚጠይቅ በጀርባው እንጨት ተሸክም ሽጦ ገንዘብ ማግኘት ይሻለዋል፡፡) እንዲሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አላህ (ዐ.ወ.) አንዳችሁ በሥራ በሚሰማራበት ወቅት በጥራት መሰራቱን ይወድለታል፡፡)

ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) እያንዳንዱ ሰው ራሱንና ወገኖቹን የሚጠቅምበት መልካም ሥራ እንድኖረው ይገፋፉ ነበር፡፡ ከዚህም አንፃር አንድህ ይላሉ፡ (ሁሉም ሙስሊም ምጽዋት መስጠት ይኖርበታል) ሰዎችም የአላህ ነብይ ሆይ! ከሌለውስ? ሲሉ ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (በእጁ ይስራና ራሱን ይጥቀም መጽዋትም ይስጥ) አሉ፡፡ እነሱም ባያገኝስ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (እገዛ የሚያስፈልገውን ሰው ጉዳይ ያውጣ) አሉ፡፡ አነሱም ባይቻለውስ? በማለት ጠየቁ፡፡ እሳቸውም (በመልካም ነገር ይዘዝ ከተንኮልም ይታቀብ ይህ ለሱ ምጽዋቱ ነው) አሉ፡፡ በዚህም ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ሥራ ባይኖረውም በሰዎች ላይ ጉዳት ከማድረስ መታቀቡ ከአላህ ዘንድ ምንዳ የሚያገኝበት መልካም ምግባር መሆኑን አስተምረውናል፡፡

ማህበረሰቡን በማገልገል፣ ደካማን በማገዝ፣ የሰውችን ጉዳይ ማውጣትና ድሆችን መርዳት ከፍተኛ ቁርጠኝነት ጥንካሬ ከሚጠይቁ ተግባራት ተቀዳሚው ነው፡፡ አንድ ቀን አንድ ሰውዬ ወደነብያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ሄደና እንድህ ሲል ጠየቀ፡ ‹የአላህ መልክተኛ ሆይ? የትኛው ሰው ነው አላህ ዘንድ በጣም ተወዳጁ የትኛውስ ሥራ ነው አላህ በጣም የሚወደው ሲል ጠየቀ፡፡ እሳቸውም ከሰወች አላህ ዘንድ ተወዳጁ ያ ከነሱ መካከል ለሰው የሚያበረክተው ጥቅም ከፍተኛ የሆነው ነው፡፡ ከአላህ ዘንድ ተዋዳጁ ሥራ ደግሞ በሙስሊም ልብ ደስታን ማስገባት፣ ወይም ከሱ ጭንቀትን ማስወገድ ወይም ለሱ እዳን መክፈል ወይም ከሱ ረሃብን ማስወገድ ነው፡፡ እኔ የውንድሜን ጉዳይ ለማውጣት ከሱ ጋር መጓዜን በዚህ መስጊድ -በመዲና መስጊድ- አንድ ወር ያህል ለዒባዳ ከመቀመጤ አብልጬ እወደዋለሁ፡፡) ቁጣውን የተቆጣጠረ አላህ ነውሩን ይደብቅለታል፡፡

ይህን ቃሌን ተናገርሁኝ ለኔና ለናንተም ከአላህ ዘንድ ምህረትን እለምናለሁ፡፡

* * *

ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአላህ እዝነትና ሰላምም በነብያትን በአላህ መላክተኞች መደምደሚያ በሰዪና ሙሐመድ በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

**ሙስሊም ወንድሞች**

ሁላችንም ለንፎካከርበትና በሱም ጠንከራ ቁርጠኝነት ሊኖረን የሚገባው እጅግ ታላቅ መስክ ደግሞ የሀገር አገልግሎት መስክ ነው፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) ለሀገር ጥቅም ባላቸው መልካም ሥራዎች እንድንፎካከር እንድህ በማለት አዞናል፡

{فَاسْتَبِقُوا الْخَيْرَاتِ إِلَى اللَّهِ مَرْجِعُكُمْ جَمِيعًا فَيُنَبِّئُكُمْ بِمَا كُنْتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ}

ትርጉሙም (በጎ ሥራዎችንም (ለመሥራት) ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡ በእርሱም ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር ይነግራችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡

አላህ (ዐ.ወ.) ለሰዎች መልካም ሥራ ለመስራት የሚጥሩ ባሪያዎቹን እንድህ በማለት አሞግሷቸዋል፡

{إِنَّهُمْ كَانُوا يُسَارِعُونَ فِي الْخَيْرَاتِ وَيَدْعُونَنَا رَغَباً وَرَهَبًا وَكَانُوا لَنَا خَاشِعِينَ}

ትርጉሙም ( እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ፡፡ ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ፡፡) ማለት ነው፡፡
የሀገር ግንባታና የማህበረሰቡን ሃላፊነት በሚገባ ለመወጣት ጠንካራ ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡ መስጊዶችን ማደስ፣ ትምህርት ቤቶችን መስራት፣ ሆስፒታሎችን ማዘጋጀት ዘላቂነት ያላቸው መልካም ሥራዎች በመሆናቸው የተቻለንን ያህል ጥረት ልናደርግባቸው ይገባል፡፡ ነብይችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (ሰባት ነገሮች አንድ ባሪያ ከሞተ በኋላ በመቃብሩም እያለ መንዳቸው ቀጣይ ይሆናል፡ አነሱም ትምህርትን ያስተማረ፣ ወንዝን የቀደደ፣ የውሃ ጉድጓድ የማሰ፣ የቴምርን ዛፍ የተከለ፣ መስጊድን የሠራ፣ ቁርአንን ያወረሰና ከሞተ ቧላ ከአላህ ዘንድ ምህረት የሚለምንለት ልጅ የተወ) የሚሉት ናቸው፡፡
ሁላችንንም ያቀፈንና ጸጋውና ትሩፋቱ መላ ነዋሪዎቹን የሚያካትት የሆነውን አገር ለማገልገል መሽቀደዳደማችን እጅጉን ደስ የሚል ነው፡፡ ይህን ተግባር በሚገባ ለማከናወን መታባበር፣ መተጋገዝ፣ መተዛዘን፣ አንድነትና ጥልቅ ግንዛቤ ያስፈልገናል፡፡

ይህን የጋራ አገራችን ለማበልጸግ በኃል፣ በጥረትና በሀሳብ ከማነም አናንስም፡፡ እኛ የስልጣኔና የታሪክ ባለቤቶች ነን፡፡ ቀዳሚነትንና የበላይነትን እውን ለማድረግ ብዙ ውጣ ውረድን እንድሁም ራስን ከቅንጦት ማራቅን የሚጠይቅ መሆኑን ጠንቅቅን ማወቅም ይጠብቅብናል፡፡ ክብር በመከራ የተከበበ ነው፡፡ ጥቅምና ደግ ነገርም በድካምና በጥረት እንጂ አይገኝም፡፡ አቡ ተማም የተባለው የግጥም ደራሴ እንድህ በማለቱ ይደነቃል፡

ታለቋን እረፍት ተመከትኩኝ የድካምን ድልድይ በማቋረጥ እንጂ የማትገኝ መሆኗንም አየሁኝ፡፡

ጌታችን ሆይኧ በሱ ቀዳሚነት፣ የበላይነት፣ እድገትና ብልጽግና የምናገኝበትን ታላቅ ቁርጠኝነትን ስጠን፡፡ ሀገራችንና የሌሎች ሀገራትንም ከመጥፎ ነገር ጠብቅልን፡፡ አሜን፡፡